# የህዳሴው ፈር ቀዳጅ

ሶፍያ ተሾመ August 13, 2015

ትግራይ ኦንላይን

ኢትዮጵያ ማስመዝገብ የቻለቻቸው ድንቅ ስኬቶች ሁሉ ላይ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር የአቶ መለስ ዜናዊ አሻራዎች በጉልህ አርፈውባቸዋል። አቶ መለስ አገራችን የመልቲ ፓርቲ ስርዓትን በመከተል ዴሞክራሲያዊ እንድትሆን አድርገዋል፤ አገራችን የፌዴራላዊ እንድትሆን በማድረግ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩና ህዝቦች በመረጧቸው ተወካዮቻቸው እንዲተዳደሩ፣ ባህላቸውንና ቋንቋቸውን እንድያጎለብቱ አድርገዋል፤ በድህነትና ጦርነት ትታወቅ የነበረችን አገር በአለም ፈጣን የኤኮኖሚ እድገት የምታስመዘግብ አገር እንድትሆን አብቅተዋታል፤ በስንዴ ልመና ትታወቅ የነበረች አገር ዛሬ ላይ በምግብ ሰብል ራሷን እንድትችል አድርገዋል፤ አገራችን በምትከተለው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዋ የዲፕሎማሲ የበላይነት እንዲኖራት በማድረግ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ መድርኮች ተሰሚነት እንዲኖራት አድርገዋል፤ አገራችን የአረንጓዴ ልማት አራማጅ እንድትሆን አድርገዋታል። ታዲያ እኛ ኢትዮጵያዊያኖች የእኚህ ታላቅ ሰው ትልቅ ውለታ አለብን።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አለም ያደነቃቸው ታላቅ መሪ ነበሩ። የአለም ታላላቅ መሪዎች፣ ፖለቲከኞች፣ ኢኮኖሚስቶች፣ የጥበብ ሰዎች፣ ወዘተ ሳይቀሩ አድናቆታቸውን ቸረዋቸዋል። እኚህ ታላቅ ሰው በሞት ሲለዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ እንዲሁም የአለም ህዝብ በጥልቅ የሃዘን ስሜት እንዲዋጥ አድርገዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከወጣትነት እድሜያቸው ጀምረው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለአገራቸውና ለህዝባቸው ሰርተዋል። ስራቸውም ውጤታማ ሆኖ አለም ስለ አገራችን መልካም መልካሙን መመስከር ችሏል።

ኢትዮጵያ ማስመዝገብ የቻለቻቸው ስኬቶች መሃንዲስ የሆኑት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩን ከህጻን እስከ አዛውንት በጥልቀት አዝኗል። ሁሉም ያዘነው ከኚህ ታላቅ ሰው ተጠቃሚ ስለነበር ነው። በወቅቱ አንዳንዶች በተለይ ጽንፈኛው የዳያስፖራ ፖለቲከኞች ህዝቡ ሃዘኑን ሲገልጽ ተገዶ እንደሆነ በማስመሰል ሲገልጹ ነበር። እነዚህ ጽንፈኛ አካላትም ቢሆኑ የፖለቲካ ትርፍ ያስገኝልናል ብለው እንጂ እውነታውን አጥተውት አልነበረም። ካፈርኩ አይመልሰኝ በሚል የተሳሳተ አካሄድ እውነታውን መሸምጠጥ የትም አያደርስም። ህዝብን አስገድደህ አደባባይ ማሰባሰብ ይቻል ይሆናል። ይሁንና በምንም ተዓምር በእንባ ልታራጨው ግን ከቶ አይቻልም።

ለሕዝብ አሳቢ፣ ብልህና ቆራጥ የሆኑት የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሕልፈተ ህይወት የኢትዮጵያዊያን ብቻ ሀዘን አልነበረም፡፡ ሕዝብን ከድህነት ማላቀቂያ ራዕያቸውን የተጋሩ፣ አስተዋይ አዕምሯቸው ባፈለቀው ሃሳብ ተጠቃሚ የሆኑ አፍሪካዊያንም ጥልቅ ሃዘናቸውን ሲገልጹ ተስትውለዋል። በቀጠባዩ ሳምንት የእኚህን ታላቅ ሰው ሶስተኛ ሙት አመት እናከብራለን።

የዛሬ ሶስት ዓመት የእኚህን ታላቅ የኢትዮጵያ መሪ ህልፈተ ህይወት ሲሰማ አለም ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን የለውን አክብሮት የገለጸው እጅግ በተለየ መልኩ ነበር። በተመሳሳይ ታላላቅ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃኖችም ስለ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዘግበዋል፡፡ በዛሬ ጽሁፌ የመራረጥኳቸውን መካከል ጥቂቶቹ እንደሚከተለው አቀረብኳቸው፡፡

***ጃኮብ ዙማ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት*** ለአፍሪካና ለኢትዮጲያ ህዝብ በአህጉራዊና በአለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ የነበሩ፣ በተካፈሉበት መድረክ ሁሉ የተለየ ብቃት ያላቸውን ታላቅ ሰውን ማጣት እጅግ አሳዛኝ ነው ። ጠ/ሚር መለስ ዜናዊ ለአገራቸው ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም ጭምር ጠንካራ መሪ ነበሩ።

***ኤለን ጆንሰን የላይቤሪያ ፕሬዚዳንት*** ጠ/ሚር መለስ ዜናዊ የኢኮኖሚ ለውጥ መሪ፣ የአህጉራቱ ምሁር መሪ ነበሩ። በአካባቢያዊ ስብሰባዎች ላይ ከአፍሪካ እደገት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ የተለየ ምሁራዊ አቅምና ብቃት ያላቸው በመሆናቸው ቀዳሚ ነበሩ።

***ባርናባ ቤንጃሚን የደቡብ ሱዳን የማስታወቂያ ሚኒስትር*** ለደቡብ ሱዳን ሪፐብሊክ ህዝብና ለምስራቅ አፍሪካ አካባቢ እጅግ በጣም አሳዛኝ ቀን ነው። ጠ/ሚር መለስ ታላቅ መሪ ነበሩ፡፡ ¸በአጎራባች አገራት ሰላም እንዲሰፍን ሁሌም የሚተጉ ነበሩ።

እኛ በደቡብ ሱዳን የምንኖር በተለይ ኢትዮጵያንና ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ምንጊዜም ወዳጃቸውን የማይከዱ በመሆናቸው እንደ አጋራችን እናስባቸዋለን። በመሆኑም በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት አዝነናል።

***ጆሰ ማኑኤል ባሮሶ የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን ፕሬዚዳንት*** ጠ/ሚር መለስ ዜናዊ የተከበሩ የአፍሪካ መሪ ነበሩ። ለአመታት ከራሳቸው አገር ህዝብ በተጨማሪ በአጠቃላይ የአፍሪካን ህዝብ ኑሮ ለማሻሻል በአፍሪካ ህብረት ፣ በአየር ንብረት ለወጥ፣ በልማት ፣ በሰላምና መረጋጋትን ዙሪያ በመስራት በተለይ በአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያረጋገጡ መሪ ነበሩ።

ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ መዳበር፣ ለሰብአዊ መብት መከበር ለህዝብ ብልፅግና እንዲሁም ለሌሎች ለአካባቢው አገራት መረጋጋትና ትስስርን የጀመረችውን ስራ አጠናክራ እንደምትቀጥል እተማመናለሁ።

***ዴቪል ካሜሮን የእንግሊዝ ጠ/ሚር*** መለስ ዜናዊ በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ የአፍሪካ ልሳን የነበሩ፣ እንዲሁም ለሱማሊያና ሱዳን አመራርና ራዕይ የለገሱ መሪ ነበሩ።

ለኢትዮጵያ ልማት በተለይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጲያውያንን ከድህነት በማውጣት ለአገራቸው ያበረከቱት አስተዋጽኦ ለአካባቢው ተምሳሌት ሆኗል። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስን አጥተናቸዋል።

***ቶኒ ብሌር የቀድሞ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር*** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በተለይ አገራቸውን ከአስከፊ ድህነት ወደ ኢኮኖሚ እድገትና ልማት እንዲሸጋገር በመምራታቸው በኢትዮጲያ ታሪክ ውስጥ የጎላ ስፍራ ያላቸው መሪ ናቸው።

***ባራክ ኦባማ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት*** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ እደገት፣ በተለይ ደሆች ኢትዮጲያዊያንን ከድህነት ለማውጣት ባላቸው ተነሳሽነት ዕውቅና ሊሰጣቸው ይገባል።

በጂ-8 አገራት ስብሰባ ላይ በተገናኘንበት ወቅት በሚሊዮን የሚቆጠር ኢትዮጲያውያንን በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ከድህነት ለማውጣት ላላቸው ፍላጎት በግሌ ያለኝን አድናቆት ገልጬላቸው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለአፍሪካ ሰላምና ደህንነት ላበረከቱት አገልገሎት፣ ለአፍሪካ ህብረት መጠናከር ላደረጉት አስተዋፅኦ፣ አፍሪካን በመወከል በዓለም አቀፍ መድረኮች ላሰሙት ድምፅ ታላቅ አክብሮት አለኝ። የኢትዮጵያ መንግስት ለልማት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለአካባቢያዊ ሰላምና መረጋጋት፣ ለሰብአዊ መብት መከበር፣ ለህዝብ ብልፅግና የሚያደርገውን ጥረት እናበረታታለን።

***ባን ኪሙን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ*** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በተለየ የአመራር ብቃታቸው የአፍሪካን ጉዳይ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በማከናወን እንዲሁም ባስመዘገቡት የኢኮኖሚ እድገት የሚታወሱ ታላቅ መሪ ናቸው፡፡

***ኦሊሴንጎነ ኦባሳንጆ የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዝዳንት*** የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት አፍሪካ ደፋርና ባለራዕይ መሪዋን የተነጠቀች ያህል የሚቆጠር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት አፍሪካን ቁርጠኛ፣ ሩቅ አሳቢ፣ ባለራዕይና ደፋር መሪ አሳጥቷታል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በዛሬይቱ አፍሪካ አንፀባራቂ ከሆኑት መሪዎች አንዱ ነበሩ፡፡

በአፍሪካ ሕብረት ያሳዩትን ስኬታማ ስራ አስተውያለሁ፡፡ መለስ ብልህ በመሆናቸው የአፍሪካ መሪዎች እኔም ጭምር የአፍሪካ ህብረትንና *የኔፓድን* ፕሮግራም እንዲያዘጋጁ ወስነን ሰጥተናቸው ነበር፡፡ ሞታቸው በጣም አስደንጋጭ ዜና ነው የሆነብኝ፡፡

***ኢስማኢል ኦማር ጉሌህ የጅቡቲ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት*** የጅቡቲ ታላቅ ወንድም የሆኑትን የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን በሞት መነጠቅ በከፍተኛ ሃዘን ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስር መለስ አገራቸውን በአፍሪካ አህጉር ከፍተኛ የኢኮኖሚ አቅም ያላት አገር እንድትሆን ለማስቻል ያደረጉት ጥረት ፍሬ መስጠት ጀምሯል፡፡ መለስ የተነሳሽነትና የቁርጠኝነት አርአያ በመሆን ሽብርተኝነትንና ፅብ አጫሪነትን በጀግንነት በመዋጋት ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር ሞት አፍሪካ ካሏት ድንቅ ልጆች አንዱን አጥታለች፡፡

***ዩዌሪ ሙሴቪኒ የኡጋንዳ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት*** የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት ኢትዮጵያ ላይ ብቻ የደረሰ አሳዛኝ ጉዳት ሳይሆን የመላው አፍሪካ ትልቅ ጉዳት ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንድነትና አገሪቱን በኢኮኖሚ ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ባበረከቱት አስተዋፅኦ ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡

ለአህጉሪቱ ሰላምና መረጋጋት እነዲሁም ለኢኮኖሚ እድገት በሚደረገው ትግል ውስጥ ታላቁን አስተማማኝ አጋር ተነጥቀናል፡፡

***ሙዋይ ኪባኪ የኬንያ ፕሬዝዳንት*** በኬንያ ሕዝብና መንግስት ስም በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተሰማኝን ጥልቅ ሀዘን ለቤተሰቦቻቸው፣ ለኢትዮጵያሕዝብና መንግስት እገልፃለሁ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አገራቸውን በማረጋጋትና በኢኮኖሚ በማሳደግ ረገድ ተጨባጭ ስራ ያከናወኑና ባለራዕይ መሪ ነበሩ፡፡

***የኬንያ ጠ/ሚር ራይላ ኦዲንጋ*** መለስ ዜናዊ ታላቅ መሪ፣ ምሁር፤ የፓን አፍሪካኒዝም አራማጅ ነበሩ። ጠ/ሚር መለስ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ወደዕድገት ለማሸገገር ባደረጉት ጥረት የሚታወሱ መሪ ናቸው።

***የቀድሞው የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሃፊ ኮፊ አናን*** የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በሕይወት አለመኖር ለኢትዮጵያ ፈታኝ ነው ፡፡ የስልጣን ሽግግሩ የተረጋጋና ሰላማዊ እንደሚሆንኸ እንዲሁም ኢትዮጵያ የሕዝቧን ፍላጎት የሚያንፀባርቅና ልዩ የሆነችውን አገር ዕምቅ አቅም የተገነዘበ መሪ እንደሚኖራት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

***የአፍሪካ ህብረት*** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለአፍሪካ ህብረት ዓላማዎች መሳካትና የአፍሪካን ፍላጎቶች በዓለም አቀፍ መድረኮች በማቅረብ ባበረከቱት አስተዋፅኦ ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በተለይ አስፈፃሚ ኮሚቴውን በሊቀመንበርነት የሚመሩት አዲስ የልማት አጋርነት በአፍሪካ (ኔፓድ) ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ በአፍሪካ መሪዎችና መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚቴ ውስጥም በብቃትና በቁርጠኝነት ሰርተዋል፡፡

የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መሪነት ኢትዮጲያ በአፍሪካ ህብረትና በኢጋድ አማካኝነት ለአፍሪካ ሰላምና ፀጥታ ላበረከተችው አስተዋፅኦ አድናቆቱን ይገልፃል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ህብረትና ለተባበሩት መንግስታት ሰላም አስከባሪ ኃየል ጦሯን በቡሩንዲ፣ ላይቤርያ፣ አቢዬ ማሰማራቷ ሳይጠቀስ አይታለፍም፡፡ ለሶማሊያ መንግስትና በሶማሊያ ለተሰማራው የአፍሪካ ሕብረት ሰላም አሰከባሪ ኃይል አሸባሪነትንና አክራሪነትን ድል ለመምታት የሚያደርገውን ጦርነት በማገዝ በአገሪቱ ዘላቂ ሰላምና ዕርቅ እንዲሰፍን ድጋፍ አድርጋለች፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ደቡብ ሱዳን ከሰሜን ሱዳን ተነጥላ የራስዋን መንግስት ከመሰረተች በኋላ የሰላም ስምምነቱና ድርድሩን ለማቀላጠፍና ተግባራዊ ለማድረግ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጥረት አድርገዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ አገራቸውን አሁን የምትገኝበት በአፍሪካ ከፈተኛ የኢኮኖሚ እድገት ስኬት እንድትበቃ በማድረግ ረገድ የላቀ ድረሻ ነበራቸው፡፡

በዚህም በኢትዮጵያና በአፍሪካ ህዳሴ የአዲስ መፃኢ ዘመን የተስፋና የዕድገት ፈርቀዳጅ በመሆን ወሳኝ ድርሻ ተጫውተዋል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት አፍሪካን ከታላላቅ ልጆቿ አንዱን አሳጥቷታል፡፡

***ዴቪድ ሺን በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር የነበ*** አብዛኞቹ የጠቅላይ ሚኒስትር ዜናዊ የመከላከያ ፖሊሲዎች አይለወጡም ብዬ እጠብቃለሁ፡፡ በአገር ውስጥ ባለው የፀጥታ ሁኔታ ለሱማሊያ ጉዳይ የሚሰጠው ትኩረት ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በኤርትራ ጉዳይ ላይ የሚወሰደውም አቋም አይለወጥም ብዬ እገምታለሁ፡፡

***በኒያሚን ናታኒያሁም የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር*** መለስ ዜናዊ በአገራቸው ጎበዝና ተወዳጅ መሪ ነበሩ፡፡ እውነተኛ የእስራኤል ወዳጅም ነበሩ፡፡ ለኢትዮጵያ ህዝብ መፅናናትን እመኛለሁ፡፡

***የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት*** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እ ኤ አ በ1990 ዎቹ 3.8 በመቶ የነበረውን የአገራቸውን የኢኮኖሚ እድገት ወደ 10 በመቶ ከፍ እንዲል በማድረግ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባሳየው እመርታ የሚደነቁ መሪ ናቸው፡፡

***ዶ/ር አርነስት ባየ ኮሮማ የሴራሊዮን ፕሬዝዳንት*** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአፍሪካ ሕብርትን ለማጠናከር የአፍሪካ ፒር ሪቪው ሜካኒዝም (peer review mechanism) ሊቀመንበር ሆነው በሰሩበት ወቅት ላሳዩት ውጤታማ ስራ፣ እንዲሁም በምስራቅ አፍሪካ ሰላም እንዲሰፍን ባከናወኑት ተግባር ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ኢትዮጰያ በአህጉሩ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበች አገር እንድትሆን አድርገዋል፡፡

***ሩቢያህ ባንዳ የቀድሞው የዛምቢያ ፕሬዝዳንት*** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለአፍሪካ ብልፅግና ያላቸውን ጠንካራ ፍላጎት ያረጋገጡ ብልህና ቅን መሪ ነበሩ፡፡ መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ እንዲሁም ለአፍሪካ በቅንነት ጠንክረው በመስራት ባበረከቱት አስተዋፅኦ ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡

***አህመድ መሃመድ ሲላንዮ የሱማሌ ላንድ ፕሬዝዳንት*** የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት ምስራቅ አፍሪካን ታላቅ ባለራዕይ መሪ አሳጥቷታል፡፡ በሱማሌ ላንድ ሕዝብና ስም እንዲሁም በግሌ ለኢትዮጰያ ሕዝብና መንግስት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞት የተሰማኝን ሃዘን እገልፃለሁ፡፡

***ቢል ጌትስ አሜሪካዊ ቢሊየነር*** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ደሃ ኢትዮጵያውያን በተጨባጭ ተጠቃሚ ያደረጉ መሪ ነበሩ፡፡ ለቤተሰቦቻቸው መፅናናትን እመኛለሁ፡፡

***የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ*** የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የእንግሊዘኛ ስርጭት አንድሪው አስሞአህ የተባሉ የደቡብ አፍሪካ የደህንነት ጥናት ኢኒስቲቲዩት ተንታኝን ጠቅሶ የሚከተለውን አስተላልፏል፡፡ "ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለአፍሪካ ራዕይ ከቆሙ ጥቂት ሰዎች መሃከል አንዱ ነበሩ፡፡ መለስ ይህ ራዕይ ምን እንደሆነ ጠንቅቀው ተገንዝበዋል፡፡ በምን አይነት አኳኋነ ወደተግባር እንደሚሸጋገርም የተረዱ መሪ ነበሩ፡፡ ምስራቅ አፍሪካ አንድ የሰላም አቋም አራማጅ የነበሩ ሰው አጥታለች፡፡"

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ወደስልጣን ከመጡ በኋላ በአገር ውስጥ የታየው የኢኮኖሚ ዕድገት ትልቁ ስኬታቸው ነው የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ ኢትዮጵያ ጠንካራና ለአፍሪካ አስፈላጊ አገር እንድትሆን አድርገዋል፡፡

***ፋይናንሻል ታይምስ*** ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የፖለቲካ መረጋጋት በማስፈንና በደሃ አገራቸው ውስጥ ላስመዘገቡት የኢኮኖሚ እድገት ዋጋ ለሚሰጡ ሁሉ አጥተዋቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከዓለም ደሃ አገራት አንዷ ብትሆንም ባለፉት ስድስት ዓመታት አማካይ አመታዊ አገራዊ ምርት እድግት 11 በመቶ ለመሆን በቅቷል፡፡ ይህም ከሳህራ በታች ካሉ አገራት አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት በላይ ነው፡፡

በርካታ የአፍሪካ አገራት ፈጣን እድገት ማስመዝገብ የቻሉት በተፈጥሮ ሃብት ላይ ተመስርተው ሲሆን ኢትዮጵያ ግን ይህ ነው የሚባል የተፈጥሮ ሀብት ሳይኖራት በአፍሪካ በኢኮኖሚ እድገት ቀዳሚዋ አገር ለመሆን በቅታለች፡፡

የሮያል አፍሪካ ሶሳየቲ ዳይሬክተር ሪቻርድ ዶውድን እንዳሉት፣ መለስ ዜናዊ አገሪቱን ሲረከቡ ሙሉ ሙሉ ኪሳራ ላይ የነበረች አገርን አሁን ላይ ለዚህ አብቅተዋታል።
ኢትዮጵያ ለወጭ ኢንቨስትመንት በሯን ከፍታለች ፣ አዲስ ያደጉትን ህንድ፣ ቱርክና ቻይና ለመሳሰሉ አገራት ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በሯን ከፍታለች፡፡ የዛኑ ያህል ከምዕራባዊያን ጋርም መልካም ግንኙነት መስርታለች፡፡

***ዴይሊ ስታር*** የኢኮኖሚ እድገት መሪ የነበሩትና አሸባሪነትን በመዋጋት የምዕራባውያንን አድናቆት ያተረፉት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በ57 አመታቸው አረፉ፡፡ መለስ ዜናዊ እ.ኤ.አ. በ1991 የመንግስቱ ኃ/ማሪያም ወታደራዊ መንግስት ስልጣን ከተረከቡ በኋላ በአፍሪካ ታዋቂ ፖለቲከኛ ወደመሆን ተሸጋግረዋል፡፡ መለስ በዓለም በድህነቷ የምትታወቀውን አገራቸውን ወደ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማሸጋገር በመቻላቸው አድናቆትን አፍረተዋል፡፡

***ኒውዮርክ ታይምስ*** በርካታ የአለም መሪዎች ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በማንሳታቸውና ለአካባቢው ሰላምና ደህንነት ላበረከቱት አስተዋፅኦ አድንቀዋቸዋል ሲል ዘግቧል፡፡ አያይዞም በአሜሪካ የውጭ

ጉዳይ መስሪያ ቤት የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ሃላፊ ጄህኒ ከርሰን የመለስ ወዳጆችም ሆኑ ተቺዎች አፍሪካ ከታላላቅ ምሁር መሪዎች አንዱን ማጣቷ ላይ ይስማማሉ ማለታቸውን ዘግቧል፡፡

***ዘ ጋርዲያን*** እ ኤ አ ከ2000 በኋላ ባሉት አመታት ኢትዮጵያ ትልቅ እድገት ማስመዝገቧና ይህ እድግት በ15 ዓመታት ውስጥ በሶስት እጥፍ የሚያድግ መሆኑ መለስ ዜናዊን ድንቅ መሪ አድርጓቸዋል፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ የስልጣን ዘመን ኢትተዮጰያ ውስጥ አዳዲስ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች በመገንባታቸው በትምህርት ዘርፍ ትልቅ ዕመርታ ተመዝግቧል፡፡ ሴቶች መብቶቻቸው ተከብረውላቸዋል፡፡ ዓለም አቀፉ የገንዘብ የቋም (አይ ኤም ኤፍ) እ ኤ አ በ2008 አንደገለፀው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከሳህራ በታች ከሚገኙ ነዳጅ አምራች አገራት በበለጠ ፍጥነት እያደገ ነው፡፡

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ የአገር መሪዎች፣ ታላላቅ ሰዎችና የህትመት ሚዲያዎች ለቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትራችን እንዲህ ያለ አስደማሚ አድናቆታቸውን የቸሩት እንደው ዝም ብለው እንዳልሆነ መገንዘብ ተገቢ ነው። እንደኔ እንደኔ ባከናወኗቸው መልካም ስራዎችና በግል ብቃታቸው እንደ አቶ መለስ አድናቆት የተቸረው አንድም የአገር መሪ አላየሁም።

አቶ መለስ እጅግ አንደበተ ርቱ ስለነበሩ በተካፈሉባቸው መድረኮች ሁሉ አድማጭን ማስደመም የሚችሉ ንግግራቸው ሁሉ ለዛ ያለው ሰው ናቸው። እውነት እውነቱን እንነጋገር ከተባለ እንኳን በመድረክ ይቅርና በየቤታችን ቴሌቭዥን መስኮት አቶ መለስ ሲናገሩ በጉጉት የማይከታተል ሰው ነበረን? አቶ መለስ በበርካታ ነገሮች ዙሪያ በቂ እውቀት ያላቸው በመሆኑ የሚሰጧቸው አስተያየቶች ሁሉ እጅግ በሳልና ገንቢ ነበሩ። በተመሳሳይ የሚያከናውኗቸው ስራዎች ሁሉ በእውቀት ላይ ተመስርተው በመሆኑ ውጤታማ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል።

***አቶ መለስ እስካሁን አገራችን ማስመዘገብ ለቻለችው ውጤት የአንበሳውን ድርሻ ነበራቸው። ይህ ብቻ አይደለም ነገም አገራችን የተሻለ እድገት ማስመዝገብ የምትችልበትን መንገድ አመላክተውናል። በመሆኑም አገራችን የጀመረችውን የህዳሴ ጉዞ ማስቀጠል የእኛ የቀሪዎቹ ተግባር ይሆናል።***